*ከታች የአዲስ ነገር ጋዜጣ የካቲት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በገጽ አምስት ያሰፈረዉን የአንጋፋዉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች፣ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ከፍተኛ የአመራር አባል የሆኑት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም በአቶ ስዬ አብርሃም ቃለ መጠይቅ ላይ ያቀረቡትን አስተያየት ከታች ለአንባቢያ አቅርበናል።*

## የአቶ ስዬ ቃለ ምልልስ
## የካቲት 10 ቀን 2000 ዓ.ም

በአዲስ ነገር ጋዜጣ የካቲት ስምንት እትማችሁ ከአቶ ስዬ ጋር ያደረጋችሁት ቃለ መጠይቅ በጣም ጥሩ  እና ለመነጋገሪያ የኾነ ጉዳዮችን የያዘ ነበር። ነገር ግን የአቶ ስዬን የወያኔነት የሥልጣን ዘመን በመጥቀስ “ቢሆን ኖሮ” በሚል አስተሳሰብን ነገርን ወደ ኋላ መጎተቱ አይጠቅምም። አንድ ሰዉ እርሱ ከነቤተሰቡ የተቀበለዉን ያህል መከራ ተቀብሎ፣ ስድስት ዓመታት በቃሊቲ ታፍኖ ቆይቶ ለማሰብ ጊዜ አልነበረዉም፤ ለመማርም እድል አልነበረዉም ለማለት ያስቸግራል። በእርግጥ ቃሊቲ የትምህርት ቤት አይደለም (የማረሚያ ቤት የሚሉት ዶሮን ሲያታልሏት ..ዓይነት ነዉ) ፤ ነገር ግን ለፈለገ ሰዉ ተቸግሮም ቢሆን በማንበብ ለመማር ይቻላል። ስዬም በእነዚህ ዓመታት ከራሱ ጋር ለመነጋገር፣ አስተሳሰቡን እና ሐሳቡን ለማጥራት ዕድል እንዳገኘ በበኩሌ አልጠራጠርም። ስለዚህም በሃይማኖት በኩል ባይሆንም በአስተሳሰብ በኩል ንስሐ እንደ ገባ በግልጽ ይታየኛል። እንኳን ሰዉ ድንጋይም ይለወጣል።

አሁን በጋዘጣችሁ እንደ ተገለጸዉ ስዬ ከዱሮዉ ጠረኝነት እና በጡንቻ ከመተማመን ወጥቶ ወደ እርቅና ወደ ሽምግልና አዘንብሏል፤ ይህ መሠረታዊ ለዉጥ ነዉ፤ ይህ የአእምሮ እና የመንፈስ እድገት ነዉ፤ የመንፈስ ልዕልና ነዉ። ሌላም ስዬ የተናገረዉ ልብ የሚነካ ነገር አለ ፤ በወያኔ የትግል ዘመናት የወደቁት እና ሕይወታቸዉን የተቀጠፉት፣ አካላቸዉ የጎደለዉ ጓደኞቹ ሁሉ ዓላማቸዉ እንዳልተሳካ በማዘን ተናግሮታል፤ ይህም የመንፈስ ልዕልና ዉጤት ነዉ። ስለ ኢትዮጵያያ እና ስለ ኤርትራ ጉዳይም መፍትሄዉ መንግስተ ሕዝብ መሆኑን ማመኑ እንደገና የመንፈስ ልዕልና ዉጤት አድርጌ አየዋለሁ።

ከሁሉ በላይ እኔን ያስደሰተኝ የስዬ አነጋገር ከቁጣ እና ከንዴት፣ ከቂም እና ከበቀል፣ ከፋከራ እና ከሸለላ የጸዳ መሆኑ ነዉ፤ የድሮዉን ስዬ እንደ እኔ በሩቅም ቢሆን ለሚያዉቀዉ የዛሬዉ ስብእና የማስመሰል ጥረት ሆኖ ሊታይ ይችላል፤ ለእኔ ግን ስጀምር የገለጽኩትን መሠረታዊ ለዉጥ በመቀበል አዲሱን ስብእና ለመቀበል አያስቸግረኝም፤ የዛሬዉን ግፍ እና መከራን የተቀበለዉ ስዬ የድሮዉ ግፍና መከራ አዳይ የነበረዉ ስዬ በዉስጡ አለ፤ ከዚህ ሰዉነትን ለሁለት ከሚከፍል የቅራኔ መድረክ ለመዉጣት ትክክለኛዉ አማራጭ ከራሱ ጋር መታረቅ ነዉ ፤ ከራሱ ጋር ለመታረቅ ደግም ከዚያኛዉ ስዬ ጋር የነበሩትን በቁጣ እና በጥላቻ ሳይሆን

ችግራቸውን በመገንዘብ እና በቅንነት መንፈስ አዲስ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው በመርዳት ነው።

የስዬ ቅን መንፈስ የሚያርፍበት ልቡና እንዲያገኝ እና ተስፋ በመቁረጥ እንዳይለወጥ ከልቤ እመኝለታለሁ፤ በምርጫው ሰሞን እኔ ለመለስ ዜናዊ የጻፍኩትን ግልጽ ደብዳቤ ፈልጎ እንዲያነብ እጋብዘዋለሁ። [1]

በመጨረሻም አንድ የምስክርነት ቃል ልስጥ፤ ስዬ የመከላከያ ሚኒስቴር በነበረበት ጊዜ የየክልሉ "ፕሬዘዳንቶች" ስብሰባ በተደረገበት ጊዜ "የኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ አለበት" ሲል ሰምቼ በጣም ተደንቄ ነበር፤ በዚያን ጊዜ ከወያኔ ባለሥልጣን የማይሰማ ሃሳብ ነበር። ይህን ጠቅሼ ከአስተያየት ጋር ለአንድ መጽሔት በመናገሬ የወያኔ ዴሞክራሲያዊ ምናምን የሚል ጋዜጣ የስድብ ናዳ አወረደብኝ።

---

[1] http://www.mesfinwoldemariam.com/docs/MWM_OpenLetter_PM_2005.pdf